5

card

በሕብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት

# ስለ ሕልውና ነክ ዓበይት ክንውኖች (Vital events) ምዝገባ

## የቤተሰብ አባሎች መመዝገቢያ ፎርም አሞላል መመሪያ

አዲስ አበባ ታሕሣሥ 1969 ዓ.ም.

316.3
ETH
MAN

በሕብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት

# ስለ ሕልውና ነክ ዓበይት ክንውኖች (Vital events) ምዝገባ

## የቤተሰብ አባሎች መመዝገቢያ ፍርም አሞላል መመሪያ

የእስታቲስቲክስ ፡ ጠ/ጽ/ቤት ፡
ቤተ መጻሕፍት
C. S. O. Library

አዲስ አበባ ታሕሣሥ 1969 ዓ.ም.

## የቤተሰብ አባሎች መመዝገቢያ ፎርም አሞላል መመሪያ

**መግቢያ:**

በኢትዮጵያ የሕልውና ነክ አበይት ክንውኖች (vital events) ምዝገባ ለማድረግ በተክኒክ፣ በሰው ኃይል፣ በአስተዳደርና በሕግ አፈጻጸም በኩል የሚያስከትለው ችግር ምን ያህል መሆኑን በቅድሚያ ለመገመት በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የሙከራ ምዝገባ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል ። ስለዚህ በአዲስ አበባ ከተማ በ16 የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትና /ማለት በ5 ከመቶ የአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ/ በሌሎች የተወሰኑ ከተሞች የነዋሪዎች ኅብረት ሥራ ማሕበራት፣ እንዲሁም በገጠር በተወሰኑ የገበሬ ማሕበራት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና፣ የፍች የሙከራ ምዝገባ ይደረጋል ።

ለሙከራ በተመረጡት ቀበሌዎች በየዓመቱ የሚወለዱት ሕጻናት፣ የሚሞቱት፣ የሚጋቡትና፣ የሚፋቱት ሰዎች ከስንት ሕዝብ ውስጥ መሆናቸውን በቅድሚያ ማወቅ ስለሚያስፈልግ ይህ የቤተሰብ አባሎች መመዝገቢያ ፎርም የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍች የሙከራ ምዝገባ በሚደረግበት ቀበሌ የሕዝቡን ብዛት በዕድሜና በጾታ ዝርዝር በቅድሚያ የሚሰበሰብበት ፎርም ነው ። የፎርሙም አሞላል ዘዴ ከዚህ በታች ተገልጾአል ።

### የመመዝገቢያ ፎርሙን አሞላል

**ዓምድ 1—3፣**

ቤተሰቡ የሚገኝበት የክፍለ ሀገር፣ የአውራጃና፣ የወረዳ ስም፣ በነዚህ ዓምዶች ጻፍ ።

**ዓምድ 4—ከተማ፣**

በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ የሚገኘው በከተማ ከሆነ የከተማውን ስም ጻፍ ።

**ዓምድ 5—የከ.ነ.ኅ.ሥ.ማ./የገ.ማ. ስም/ቁ.፣**

የከ.ነ.ኅ.ሥ.ማ./የገ.ማ.ስም/ቁ. ማለት የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም የገበሬ ማሕበር ስም ወይም ቁጥር ማለት ነው ። በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ የሚገኘው ከተማ ከሆነ የከተማው ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማሕበር፣ ገጠር ከሆነ ደግሞ የገበሬ ማህበር ስም ጻፍ ። የከተማ ነዋሪዎች የሕብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙባቸው ከተሞች ቀበሌዎች የተለየ ስም ከሌላቸው ለያንዳንዱ ቀበሌ በቀበሌው ጽ/ቤት የተሰጠው የመለዩ ቁጥር ጻፍ ። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከተማ የተቋቋሙ-የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማሕበራት ለያንዳንዱ ቀበሌ ባለስድስት አሀዝ መለዩ ቁጥር ተሰጥቶታል ። የመጀመሪያው ሁለት አሀዝ የወረዳው፣ ቀጥሎ ያለው ሁለት አሀዝ የንዑስ ወረዳው፣ የመጨረሻው ሁለት አሀዝ ደግሞ የቀበሌው ይሆናል ። የቀበሌው የመለዩ ቁጥሩ ከቀበሌው ጽ/ቤት ወይም ከያንዳንዱ ቤት ለማግኘት ይቻላል ።

**ዓምድ 6፣ የከ.ነ.ኅ.ሥ./የገ.ማ. ሊቀመንበር ስም፣**


በዚህ ዓምድ ቤተሰቡ የሚገኘው ከተማ ከሆነ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማሕበር ሊቀመንበር፣ ገጠር ከሆነ ደግሞ የገበሬ ማሕበር ሊቀመንበር ስም ጻፍ ።

../..

ሚስቶች እንደ ልዩ ቤተሰብ መቆጠር አለባቸው ፡፡ በዚህ ሁኔታ ባልየው አሁን ካላቸው
አንጋፋዋ ሚስት ጋር ይሁን ፡፡ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ወዘተ. ሚስቶች ግን የየራሳቸው ቤተ
ሰብ አላቸው ማለት ነው ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አንዱን ቤተሰብ በትክክል ለመለየት ያስቸግር ይሆናል ፡፡ ዋናው
ን ነገር ማስታወስ ያለብን የአንድ ቤተሰብ አባሎች ምግባቸውን አብረው የሚያበስሉትና
የሚካፈሉት መሆናቸውን ነው ፡፡ በአንዳንድ ከተሞች ብዙ ወንዶች ወይም ሴቶች አንድ
ቤት ተጋርተው የሚኖሩ አናገኝ ይሆናል ፡፡ እነኚህ ሰዎች እንደ አንድ ቤተሰብ የሚቆ
ጠሩት ምግባቸውን አንድ ላይ አብስለው ሲበሉት ብቻ ነው ፡፡ ስለዚህ የቤተሰብ ትርጉም
ለይተህና ጠንቅቀህ ካወቅህ በኋላ በዓምድ 8 ለያንዳንዱ ከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ
ማሕበር የሚገኝ ቤተሰብ ቁጥር ጻፍ ፡፡ በመጀመሪያው ለምታገኘው ቤተሰብ 0001፣ ለሁ
ለተኛ 0002፣ ወዘተ. እየሰጠህ እስከ መጨረሻው ቤተሰብ በቀደም ተከተል ቁጥር ጻፍ
ላቸው ፡፡ የሚከተለውን የቁጥር አሰጣጥ አጀማመር ዘዴ ተመልከት ፡፡

ከዚህ ጀምር



ወዘተ.........

<u>ማሳሰቢያ</u>

የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራዎች ማለት እስር ቤቶች፣ የሙት ልጆች የሚኖሩበት፣ አ
ድባራት፣ ገዳማት፣ የወታደር ሠፈሮች ሆስቴሎች፣ ሆቴሎች አዳሪ ት/ቤቶች ወዘተ. ያጋ
ጠሙህ እንደሆነ በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራ ስም ብቻ ጻፍ ፡፡ በጋርዮሽ መኖ
ሪያ ሥፍራዎች ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች ግን በዓምድ 8 ቁጥር ጻፍላቸው ፡፡

<u>ዓምድ 9—ተራ ቁጥር፣</u>

በዚህ ዓምድ ላይ የሚገኙ ቁጥሮች አስቀድሞ ለ10 ወይም ከዚያ በታች ላነሱ
የቤተሰብ አባሎች ታትሞአል ፡፡ ነገር ግን የቤተሰቡ አባሎች ቁጥር ከ10 በላይ ከሆነ
አዲስ ፎርም መጠቀም አለብህ ፡፡ በዚህ በአዲሱ ፎርም በአንደኛው ፎርም በዓምድ 1—8
የሞላኻቸው እንደገና ገልብጠህ ከጻፍክ በኋላ ዓምድ 9 በታተመው ቁጥር ማለት በ01
ላይ 11፣ በ02 ላይ 12 ወዘተ. እየጻፍክ የቤተሰቡ አባሎች በሙሉ መዝግብ ፡፡

<u>ዓምድ 10—የቤተሰቡ ቋሚ አባሎች ሙሉ ስም፣</u>

የቤተሰቡ ቋሚ አባሎች የሚባሉ ከዚህ በታች ተመልክተዋል ፡፡

.../...

ዓምድ 19– የቆጣሪው ስምና ፊርማ

በዚህ ዓምድ ከዓምድ 1 ጀምሮ እስከ ዓምድ 15 የሞላ ቆጣሪ ስሙንና ፊርማውን መጻፍ አለበት ::

ዓምድ 20– ቀን ወርና ዓመተ ምሕረት

በዚህ ዓምድ ቆጣሪው በዓምድ 1 እስከ ዓምድ 15 የሞላበትን ቀን ወርና ዓመተ ምሕረት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በአኃዝ መጻፍ አለበት ::

ዓምድ 21–23፤

የቤተሰቡ አባሎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከተመዘገቡ በኋላ ወደ ቤተሰቡ በየጊዜው የሚከናወን የጉብኝት ሁኔታ የሚያመለክቱ ዓምዶች ናቸው :: ከዓምድ 16 እስከ ዓምድ 18 ለጊዜው ስለማይሞሉ፤ ይህ ቆጠራ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በየሶስት ወር ቤተሰቡ በድጋሚ ስለሚጎበኝ በቤተሰቡ አባሎች ዝርዝር የሆነውን ለውጥ ከአለ በነዚህ ዓምዶች ይገለጻልና በዓምድ 21–23 አስፈላጊውን በዚያን ጊዜ ይሞላል :: ስለዚህ ዓምድ 21–23 ይህ ቆጠራ ከተከናወነ ከሦስት ወር በኋላ የሚሞሉ ስለሆነ እናንተን አይመለከቱም ::

ዓምድ 21– የጉብኝቱ ብዛት

በዚህ ዓምድ 1 እስከ 8 ቁጥሮች ተጽፈዋል :: ወደያንዳንዱ ቤተሰብ የሚደረገው ጉብኝት በየሶስት ወር አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል :: ስለዚህ በዚህ ዓምድ 1 ማለት የመጀመሪያው ሦስት ወር፤ 2 የሁለተኛው ሦስት ወር፤ ወዘተ. ማለት ነው ::

ዓምድ 22– ጉብኝቱ የተደረገበት ቀን ወርና ዓመተ ምሕረት

በዚህ ዓምድ በየሦስት ወር የሚፈጸም ጉብኝት ቀኑን ወሩንና ዓመተ ምሕረቱን ይጻፋል ::

ዓምድ 23– የጉብኝው ፊርማ

በየሦስት ወር ወደ ቤተሰቡ ጉብኝት በሚደረግበት ጊዜ በዚህ ዓምድ የጉብኝው ፊርማ መጻፍ አለበት ::

Date Due